دار زايد للثقافة الإسلامية
Zayed House For Islamic Culture

# አይቻልም ተብሎ የሚታሰብን ነገር የማሰካት ጉጉት

ፀሐፊ ፡ ሸይኻ ናስር አል-ከርቢ

“ጡሙሕ/ትልቅ ምኞት፣ ከፍተኛ ጉጉት” የሚለውን ቃል ምትሃታዊ ልንለው እንችላለን፤ እኛ ከማንፈልገው ተጨባጭ ጋር ለማይጣጣመው ሁኔታ እጅ ባለመስጠት ከፍ ወዳለ፣ ወደፊት የሚያስኬድ እና ምኞትን ወደማሳካት የሚወስድ ሁኔታ ነው። በተለይም ይህ ጉጉት የማይሳካ የሚመስል ዓይነት ከሆነ ሁሉንም ተስፋን ይዞ ሊያጋጥሙ የሚችሉ መላምቶችን ተራምዶ የመጓዝ ከፍተኛ ፍላጎት ነው።

ግልፅ የሆነ፣ ጠንካራ፣ ተጨባጭን ያገናዘበ፣ ጤናማ ዕውቀት፣ እና ጠንካራ ሀሳብ ያለው ጉጉ ሰው ራሱን ለማሳደግ ሁሌም ትግል ውስጥ ነው። ግልፅ የሆነ አቅጣጫ ያስቀምጣል፤ በአቅጣጫውም አማካይነት ምኞቱን ያሳካል፤ ሊደርስበት የሚፈልገው ቦታ መድረሱ የማይታሰብ የሚመስል ቢሆን እንኳ እየታገለ እና እየተቃወመ ይጓዛል። እሱ ከርሱ ጋር በተመሳሳይ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ያሉ ባልደረቦቹም ሆኑ ሌሎች እንደሚያስቡት አይደለም።

ግልፅ በሆነ ፍላጎትና ጉጉት፣ ብርቱ ፅናትና ቁርጠኝነት የሰው ልጅ “አይቻልም” የሚለውን ቃል ማስወገድ ይችላል። በዚህም በሕይወት ዘመኑ ፊትለፊቱ የሚቆም ነገር አይኖርም። በዓላማው፣ በጠንካራ ፅናቱ፣ በፍላጎትና በራስ በመተማመን መንፈስ የ”አይቻልምን” ቅዠት በመስበር የማይታይ የነበረውን እሩቅ ነገር የሚታይ ተጨባጭ በማድረግ ያሳካዋል።

ይህን ሁሉ ለማሳካት ግን ከዚያ በፊት የሚያስፈልገው ነገር አለ። በትዕግስት መዋብ፣ መከራን መሸከም፣ በዓላማ ማመን፣ ፅኑ ፍላጎት፣ መልካም መርህና ሥነምግባር ያስፈልጋል። ትዕግስት የጉጉ/ከፍ ያለ ዓላማ ያለው ሰው የመጀመርያ ባህሪ ነው። ህልም በአንድ ጀንበር የሚሳካ አይደለም። ትልቅ ጥንካሬን፣ ብርታትን፣ ጤናማ በሆነ መልኩ ማቀድን፣ ጥልቅ ዕውቀትን፣ ከስኬታማዎች ጋር መቀማመጥን፣የራስህን ክህሎት ማሳደግን ይጠይቃል።

መልካም መርህ እና ሥነምግባር ዓላማን ከማሳካትና ለግለሰብም ሆነ ለማኅበረሰብ ጥቅምን ከማረጋገጥ ዋንኛ መሣርያዎች ናቸው። ስኬት መመዘን ያለበት ለማኅበረሰቡ ከሚያስገኘው ደስታ አንፃር ነው። የአንድ ሰው መልካም ምኞቱን የማሳካት ጉጉት ለማኅረሰቡም ጥቅምና ፋይዳ ያስገኛል።

በመሠረቱ ዓላማዎች ለማሳካት የሚችሉ ዓይነት መሆን አለባቸው። የማይጨበጡና ባልተጠና መሠረት ላይ የተገነቡ መሆን የለባቸውም። ከፍተኛ

ምኞትና ጉጉት ያለው ሰው ካሰበው ለመድረስ ይሮጣል፣ ይታገላል፣ ለዓላማው ሲንቀሳቀስም  በሚሠራው ሥራ ይደሠታል፣ ይዝናናል፤  "ከጉጉት ጋር የማይሳካ ነገር የለም" የሚለው መፈክሩ ሁልጊዜም ዐይኑ ላይ ነው።